# (መጽሐፈ ኢያሱ)

## ጥናት አንድ ኢያሱ ማን ነው?(ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እያንዳንዱ በራሱ መንገድ ምንባቡን ያስረዳ፡፡
2. ኢያሱ ከማዘዝ በፊት መታዘዝን መማሩ እግዚአብሄር ሊጠቀምበት የሚያመች ጥሩ አገልጋይ ይወጣዋል፡፡ እኛም ጥማታችን የበላይነትና ማዘዝ ሳይሆን በመጀመሪያ ለመታዘዝ የምንችልበት ትህትና ልንለብስ እንደሚያስፈልገን እንማራለን፡፡
3. እግዚአብሄር ኢያሱ መስማቱን ማረጋገጥ የፈለገው ሃሳብ ጦርነት በገዛ ጉልበትና በመሳሪያ ብዛት መካሄድ ያለበት ነገር ሳይሆን እጅን ወደ አምላክ በማንሳት በእርሱ ላይ በመደገፍ መካሄድ ያለበት ነገር እንደሆነ እንዲሰማ ነው፡፡ በተለይ ለኢያሱ አስፈላጊ ሆኖ የሚገኘው ከፊቱ ቁጥር የሌለው ጦርነት ስለሚጠብቀውና ስለ አማሌቅ ደግሞ እግዚአብሄር የተናገረውን አስፈጻሚ እርሱ ስለሆነ ነው፡፡
4. ሙሴ፤ ኢያሱ፤ ሽማግሌዎቹ፤ አሮን፤ ሖር፤ እስራኤላውያን፡፡
5. ወደ እግዚአብሄር ተራራ የወጡት ሙሴና አገልጋዩ ኢያሱ ናቸው፡፡ በተለይ የኢያሱ ወደ ተራራው መውጣት ከለሎቹ የሚለየው፡ የወርቁን ጥጃ በማምለክ ራሱን እንዳያረክስ ተጠብቋል፤ ለአርባ ቀንና ለአርባ ሌሊት የእግዚአብሄርን ክብር ማየትና ድምጹን የመስማት እድል ነበረው፡፡
6. 2ኛ ጴጥ 1፡16-18 እንደሚናገረን በአዲስ ኪዳን በተራራው ላይ የኢየሱስን ክብር እንዳዩት ሶስቱ ሃዋርያት ኢያሱም ከሰዎች በሰማው ብቻ ሳይሆን ስለ እግዚአብሄር ክብርና ማንነት የአይን ምስክር ስለሆነ በድፍረት ለመናገር ያስችለዋል፡፡
7. በዚህ ክፍል የምናያቸው፡ ኤልዳድ፤ ሞዳድ፤ አንድ ወጣት፤ ኢያሱ፤ ሙሴና ሽማግሌዎች፡፡ ኢያሱ ሙሴን ሊመክርና ሃሳብ ሲሰጥ እናየዋለን፤ ሆኖም የኢያሱ አመለካከት የተሳሳተ በመሆኑ ሙሴ እንዲያስተካክል ሲመክረው ይታያል፡፡
8. የኢያሱ ያደረገው ስህተት ማናቸውም ሰው ሊሳሳተተው የሚችለው ሲሆን ስህተቱ በሙሴ ዛሬ ባይታረም ቆይቶ ትልቅ ቦታ ከያዘ በኂላ ከሱ በታች በሆኑት ለመታረም ምናልባት ሊቸግረው ይችል ነበረ፡፡
9. እያንዳንዱ የራሱን መስስ ይመልስ፡፡

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት ሁለት (ኢያሱ 1፡1-9)

1. ባሪያው ሙሴ እንደሞተ፤ ህዝቡና ኢያሱ ዮርዳኖስን እንዲሻገሩ፤ የእገራቸው ጫማ የረገጠውን ቦታ ሁሉ እንደሚሰጣቸው፤ የርስት ዳርቻቸውን ክልል…
2. ሙሴ ያልተጀመረ ሥራ እንዲጀምር ሲሆን ኢያሱ የተጀመረ እንዲፈጽም፤ለሙሴ ራሱን ማስተዋወቅ ነበረበት ለኢያሱ አላስተዋወቀም፤ የሙሴ ጥሪ ለማስወጣት ዘጸ4፡10 የኢያሱ ለማስገባት፤ኢያ1፤6፤ ሙሴ ተከራከረ ኢያሱ አልተከራከረም…
3. ኢያሱ የሚያደርገውን ሁሉ ያደርግ የነበረው ሙሴ እየነገረውና እየመራው ስለነበረ አሁን ነገሮችን በራሱ ማድረግ እንዲጀምር ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ የሞተው የእግዚአብሄር ባሪያ እንጂ እግዚአብሄር ስላልሆነ የሥራው ጌታ የሚያሰማራው እንደማያጣ እንዲያውቅ ነው፡፡
4. ‹‹…እግራችሁ የሚረግጠውን ቦታ ሁሉ እሰጣችኋለሁ›› የሚለው እግዚአብሄር በሰጠው ክልል ይወሰናል፤ ማትም በዚያ ክልል ውስጥ ያለ ማናቸውም የሚረግጡትን ቦታ ይወርሳሉ ያልረገጡት ደግሞ ክልላቸውም ቢሆን ይቀራል፡፡
5. አብርሃም፤ ይስሃቅ፤ ያዕቆብና የዮሴፍ እድሜ ስደመር ብቻ ቢያንስ
6. ስንት ጦረኞች እንደሚያሰልፍ፤ በየት አቅጣጫ መሄድ እንዳለበት፤ የሚያስፈልገው የመሳሪያ አይነትና ብዛት…ወዘተ ሲሆን እግዚአብሄር የመከረው ምክር ግን፤ ጦርነቱ እንደሚገባው እንዲካሄድና ድል እንዲገኝ ካስፈለገ ኢያሱ ከእግዚአብሄር ጋራ ላለው ግንኙነት የተለየ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባው፡፡ በዚህ ክፍል መከናወን የተያያዘው ቃሉን ከማሰላሰልና ከመታዘዝ ጋራ ነው፡፡
7. የዮርዳኖስ ጢም ብሎ እስከ አፍጢሙ መሙላት፤ ሊዋጓቸው ያሉት ነገሥታት ብዛት፤ የሙሴ አብሮት አለመኖር፤ ከሙሴ ጋራ በማወዳደር በህዝቡ ዘንድ የሚኖረው ተቀባይነትና የመሳሰሉት፡፡
8. ለፍርሃት መልስ ሆኖ የቀረበው ሃሳብ እግዚአብሄር አምላክህ ከአንተ ጋራ ስለሆነ አትፍራ የሚለው ነው፡፡ ቁ9   መዝ 56፡3
9. እያንዳንዱ ሃሳብ እንዲሰጥ በየተራ በየተራ ለማዳረስ ይሞክር፡፡

# <u>ለመሪው የተዘጋጀ</u>

## <u>ጥናት ሶስት (ኢያሱ 1፡10-18)</u>

1. ህዝቡ እንዲሰሙት የፈለገው ነገር በሶስት ቀናት ውስጥ ወደተስፋይቱ ምድር ስለሚገቡ ስንቃቸውን እንዲሰንቁና ዝግጅቱን እንዲያደርጉ ሲሆን ዜናውን ለማድረስ ሃላፊነቱን የተቀበሉት የህዝቡ አለቆች ነበሩ፡፡
2. አዎን ሰርቶለታል፤ ምክንያቱም ኢያሱ ወዲያው ቀድሞ አድርጎትና ተለማምዶት የማያውቀውን አዲስ ነገር ሲያደርግ በቁ10 ላይ እናየዋለን፤ ይኸውም ከህዝቡ አልፎ ለአለቆች በድፍረት ትዕዛዝ መስጠቱ ተልዕኮውን መቀበሉን ያረጋግጥልናል፡፡
3. ‹‹…ገብታችሁ ትወርሳላችሁ፡፡›› ከሚለው አነጋገር ለኢያሱ እግዚአብሄር አንድ ነገር ተናገረ ማለት ተከናወነ ወይም ሆነ ማለት መሆኑን የተረዳ ሰው መሆኑ ይታያል፡፡
4. ምክንያቱም እነዚህ ሁለት ነገድ ተኩሎቹ አስቀድሞ ሙሴ ሳይሞት ዮርዳኖስን ሳይሻገሩ ከዮርዳኖስ በስተምስራቅ ባለው ቦታ እንዲሰፍሩ ፈቅዶላቸው ስለነበረና ያ ምድር ደግሞ በእስራኤል ቁጥጥር ስር የዋለ በመሆኑ እነሱ መሻገር ስለማይኖርባቸው ነው፡፡
5. ከዚህ የምንማረው ጥሩ መሪ በተሰራው መልካም ነገር ላይ የሚገነባ እንጂ ሥልጣኑን ለማሳየት ብቻ የተሰራውን ሁሉ አፍርሶ የራሱን መገንባት ማለት እንዳልሆነ ነው፡፡
6. ለሁለቱ ነገዶች ተኩል የተሰጠው መመሪያ፤- የሙሴን ትዕዛዝ እንዲያስቡ(13)፤ ቤተሰቦቻቸውና ንብረታቸው እንዲቆዩና እነርሱ ግን ከወንድሞቻቸው ጋራ ለውጊያ እንዲሰለፉ ሲሆን እነሱም መመሪያውን የተቀበሉት በሙሉ ልብና እሺታ ነበረ፡፡
7. እግዚአብሄር ቃል የገባላቸውን ርስት እንዲወርሱ የልብ ልብና ድፍረት ይሆናቸዋል፡፡ ይህንን ባያደርጉ ግን እግዚአብሄር የህዝቡን ልብ ካቀለጡትና ከተቆጣቸው ከአስሩ ሰላዮች ለይቶ እንደማያያቸው ዘኁ 32 ግልጽ ያደርግልናል፡፡
8. በሥራ መተርጎም የእያንዳንዱ ሃላፊነት መሆኑ ይገለጽ፡፡

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት አራት (ኢያሱ 2፡1-24)

1. ኢያሱ፣ ሁለት ሰላዮች፣ ረዓብ፣ የኢያሪኮ ንጉሥ እና የንጉሡ መልዕክተኞች፣፣ የሰላዮቹን ተልዕኮ ስውር ያደረገበት ምክንያት ምናልባት ሪፖርቱን ይዘው ሲመጡ በሙሴ ጊዜ እንደሆነው የህዝቡ ልብ እንዳይቀልጥ ከቀደመው ስህተታቸው የተማረው ነገር ይሆናል፡፡
2. እግዚአብሄር ምድሪቱን ለእስራኤል እንደሰጠ፣ እስራኤልን መፍራት በኢያሪኮ ነዋሪዎች እንደወደቀና ነዋሪዎቹ በፍርሃት ልባቸው መቅለጡን ነገረቻቸው፡፡
3. የህዝቡን ልብ ያቀለጠው በቁ10 ላይ የተናገረችው የቀይ ባህር መከፈልና የአሞራዊያን ነገሥታት ድል መመታት ናቸው፡፡
4. ቀይ ባህርን አሻግራለሁ ብሎ ያሻገረን፣ እዋገላችኋለሁ ብሎ ከአሞራዊያን ጋራ የተዋጋልን አምላክ ዛሬም አወርሳችኋለሁ ያለንን ኢያሪኮን ሊያወርሰን ታማኝ ነው ለማለት ያስችላቸዋል፡፡
5. የኢያሪኮ ህዝብ የሰሙትን እውነት ለፍርሃት ሲያውሉት ረዓብ ግን እውነትን ሰምታ የእምነት እርምጃን በመራመድ ለመዳኗ ተጠቀመችበት፡፡ ከዚህ የምንማረው ስለ እግዚአብሄር የምንማረው ነገር ወደ እርሱ የሚያቀርበን እንጂ እንድንፈራውና ከእርሱ እንድንርቅ ሊያደርገን እንደማይገባን ነው፡፡
6. 1፡11 ‹‹ገብታችሁ ትወርሳላችሁ›› 2፡14 ‹‹ምድሪቱን በሚሰጠን ጊዜ›› እነዚህ አባባሎች ከገባን ወይም ከሰጠን ሳይሆን የማይቀር ነገር እንደሆነና የጊዜ ጉዳይ እንደሆነ ሁለቱም የተቀበሉት እውነት መሆኑን እንረዳለን፡፡
7. በዘኍ ሰላዬቹ ሪፖርቱን ያቀረቡት ለህዝቡ ሁሉ ሲሆን በኢያሱ ውስጥ ግን ሪፖርቱ የቀረበው ለኢያሱ ብቻ ነበረ፡፡ ይህም በሙሴ ጊዘ የተፈጠረው አይነት አመጽ እንዳይደገም ይረዳል፡፡
8. እያንዳንዱ የግሉን ለራሱ ይመልስ

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት አምስት (ኢያሱ 3፡1-17)

1. ካህናቱ የእግዚአብሄርን ቃል ኪዳን ታቦት ተሸክመው ሲያዩ ታቦቱን እንዲከተሉ፤ በታቦቱና በህዝቡ መሃል ሁለት ሺህ ክንድ ርቀት እንዲኖር፤ ወደ ታቦቱ እንዳይቀርቡ።
2. እኛም ብንሆን የእግዚአብሄር ማንነት በህይወታቸው የሚገለጥና በህይወታቸው ምሳሌነት ሊመሩን የሚችሉትን ሰዎች የምንከተል ሰዎች ልንሆን ይገባናል።
3. ቀይ ባህርን ለመክፈል የተጠቀመው ሙሴንና በትሩን ሲሆን ዮርዳኖስን ለመክፈል ደግሞ ካህናቱንና ታቦቱን ነበረ፤ ቀይ ባህር ላይ ህዝቡ እንዲሄዱ በዮርዳኖስ ደግሞ ታቦት እንዲያስቀድሙ…ወዘተ። ከእግዚአብሄር ሁለት ተመሳሳይ ችግሮች ቢኖሩን ሁልጊዜ በአንድ መንገድ መፍትሄ ያመጣል በማለት አሰራሩን አጥብበን ማየት እንደማይገባንና እግዚአብሄር በወደደው መንገድ መሥራት እንደሚችል እንማራለን።
4. በዘዳ 14 ውስጥ የእስራኤል ህዝብ ባህሩ ሲከፈል ቀጥ ብሎ የመግባት እንጂ የመጠበቅ ልምድ የለውም፤ የተከፈለ ውሃ ለመሻገር ታቦት መከተል አዲስ አሰራር ነው፡
5. በዚህ ክፍል ለእግዚአብሄር ያላቸውን ቅርበት የወሰነው እግዚአብሄር ራሱ ሲሆን፤ አዲስ ኪዳን ግን ቅርበታችንን የምንወስነው እኛ እንደሆንን እናያለን። ዕብ 10፡22፤ ያዕ 4፡8
6. ለዚህ ማረጋገጫ ሆኖ የተሰጣቸው ነገር፤ የምድር ሁሉ ጌታ የቃል ኪዳኑ ታቦት ቀድሚቸው ወደ ዮርዳኖስ መግባቱ ነው። በእኛም ህይወት ቢሆን እግዚአብሄር በሁኔታችን ውስጥ ቀድሞ ከገባልን በድል እንደምንወጣ የማያጠራጥር ነገር ነው።
7. ለእግዚአብሄር የውሃ መሙላትና መጉደል ምንም ልዩነት አያመጣም፤ ነገር ግን እስራኤላውያን ዘወትር የእግዚአብሄር ፍርሃት እንዲኖራቸውና ጠላቶቻቸው ደግሞ የእግዚአብሄርን እጅ ታላቅ እንደሆነች እንዲያውቁ። 4፡24
8. እያንዳንዱ የራሱን መልስ ይስጥ።

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት ስድስት (ኢያሱ 4፡1-24)

1. ከየነገዱ አንዳንድ ሰው እንዲመርጥ፤ ከዮርዳኖስ ወንዝ ካህናቱ ከቆሙበት ሥፍራ አሥራ ሁለት ድንጋይ እንዲወስዱ፤ የዚያን ቀን በሚያድሩበት ቦታ እንዲያኖሯቸው።
2. ከዮርዳኖስ ወንዝ መካከል ልክ ካህናቱ ከቆሙበት ሥፍራ ነበረ። እግዚአብሔር እዚህ ላይ ማተኮሩ የዮርዳኖስ ወንዝ መድረቁ ምክንያት የታቦቱ ወይም የእግዚአብሔር በውሃው መሃል መገኘት መሆኑን እንዳይዘነጉት ማሳሰቢያ ይሆናል።
3. እግዚአብሔር ፍጥረታችንን ስለሚያውቅ በድካማቸው እየረዳቸው ነው። ለእግዚአብሔር የገባነውን የሠርግ ቃል ኪዳናችንን እንኳን ከምኔው ዘንግተን እርስ በእርሳችን ምን ያህል መጎዳዳት ውስጥ እንደምንገባ ስናስብ ምን ያህል ዝንጉ እንደሆንን እንረዳለን።
4. ወደፊት ልጆቻችሁ ሲጠይቋችሁ እንዲህ ብላችሁ መልሱ የሚለው ሃሳብ፤ እግዚአብሔር እንደ እኛ ዛሬ በሚካሄደው ነገር ወየም ደግሞ በራሳችን ላይ ብቻ ማተኮር እንደማይኖርብን ነገር ግን ስለ ልጆቻችንና ስለ ልጅ ልጆቻችን ሁሉ አርቀን ማሰብ እንደሚገባን እንማራን።
5. እነዚህ ሰዎች በኢያሱ 1 ላይ ለኢያሱ ወንድሞቻቸውን እንደሚረዱ ቃል ገብተውለት እንደነበረ እንመለከታለን። በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የምናየው ደግሞ እነደተናገሩት ቀድመው ከወንድሞቻቸው ፊት ለጦርነት ሲዘጋጁና ቃላቸውን ሲጠብቁ ነው።
6. በቁ21-22 ያለው ክፍል የልጆች ጥያቄ የሚሰነዘረው በተለይ ወደ አባት እንደሆነ ይጠቁመናል። ከዚህ የምንማረው በተለይ አባቶች ለልጆቻቸው መንፈሳዊ ነገርን ለማስረዳት ማዕከላዊውን ሥፍራ ሊወስዱ እንደሚገባቸው እንማራለን።
7. ቀይ ባህርንና የዮርዳኖስን ወንዝ ያደረቀባቸው ምክንያቶች፡ አንዱ የእግዚአብሔር ክንድ ብርቱ መሆኑን አህዛብ ሁሉ እንዲያውቁና ሁለተኛው ደግሞ እስራኤል ሁሉ ለዘላለም አምላካቸውን እግዚአብሔርን እንዲፈሩ ነው።
8. የእርሱን ማንነትና ድንቅ ሥራውን ለልጆቻችን አለማስተላለፍ እግዚአብሔርን የማያውቅና የማይፈራ ትውልድ የሚበቅልበት ለምለም መሬት እንደማዘጋጀት ይሆናል። የተቀረው ጥያቄ የግል ሃሳብ ይሰጥበት።

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት ሰባት (ኢያሱ 5፡1-15)

1. ከዮርዳኖስ በስተ ምዕራብ ያሉት ነገስታት ሁሉ የዮርዳኖስን መከፈል ሲሰሙ ፍርሃት እንደወደቀባቸውና ልባቸው እንደቀለጠ ይናገራል፡፡ ይህም በመሆኑ እግዚአብሄር በ4፡24 ላይ ካቀደው እቅዱ የመጀመሪያው ወዲያውኑ ግብ እንደመታለት እንመለከታለን፡፡
2. ከግብጽ የወጡት ወንዶች ሁሉ ተገርዘው ነበረ፤ ሆኖም እግዝአብሄርን ስላስቆጡት በምድረበዳ ውስጥ ሞተው ስላለቁ አዲስ የተወለደው ወጣት ግን ስላልተገረዘ ለዚህ ነው ሁለተኛ ግርዛት ያስፈለገው፡፡
3. በሰው አመለካከት በዚህ ጊዜ መግረዝ ስሜት አይሰጥም፤ ምክንያቱም የሰፈሩት በቁ10 መሰረት ከጠላቶቻቸው ሰፈር ውስጥ ስለሆኑ ቁስላቸው ሳይሽር መጥተው ሊጨርሷቸው ይችላሉ፡፡ ዘፍ 34፡24-25ትን መመልከት ይረዳል፡፡
4. ኢያሱ ሁኔታውን ሳይረዳ ቀርቶ ሳይሆን ድል የሚገኘው በሰራዊት ብዛት ወይም ከጦር ከዝግጅትና ቅንጅት ሳይሆን ድልን ሊሰጥ በሚችለው በእግዚአብሄር ላይ በመደገፍ መሆኑን ስለተረዳ ነው፡፡
5. መና መብላት ያቆሙት የከነዓንን ምድር ፍሬ በበሉበት ቀን ነው፡፡ በመናው መቆም ደስተኞች የሚሆኑ ነው የሚመስለኝ ምክንያቱም ዘኁ 11፡4-6 ገና ድሮ ያጉረመረሙበት ነገር ስለሆን እስከዛሬ መብላታቸው ግድ ሆኖባቸው ነው፡፡ እኛም ጊታ አስከፊ ጊዜን እንድናልፍ ያዘጋጀልንን ነገር እንደበረከት ወስደን ማመስገኛ እንጂ የተሸለ የሚመስል ነገር ስናገኝ የምንንቀው እንዳንሆን፡፡ ምሳሌ፡ ቀድሞ የደከመ መኪና ከነበረንና ዛሬ አዲስ መኪና ካወጣን፤ ትናንት ከሰው ተጠግተን ኖረን ዛሬ የራሳችን ቤት ሲኖረንና የመሳሰሉትን ማሰብ ይቻላል፡፡
6. የመጀመሪያው ‹‹ከእኛ ወገን ነህ ወይስ ከጠላቶቻችን?›› ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ‹‹ጌታዬ ለባሪያው የሚነግረው ምንድነው?›› በተለይ ለሁለተኛው ጥያቄ የተሰጠው መልስ ‹‹ጫማህን ከእግርህ አውልቅ፤ የቆምክባት ምድር የተቀደሰች ናትና፡፡›› ይህ መልስ የሚያስተምረን ከጦር ዝግጅት በፊት መንፈሳዊ ዝግጅት እንደሚቀድም ነው፡፡
7. በእግዚአብሄር ማዳን ላይ ያለው እምነት ምን ያህል ጠንካራ እንደሆነ ያስተምራል፡፡ የተቀረውን ጥያቄ እያንዳንዱ የራሱን መልስ ይስጥበት፡፡

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት ስምንት (ኢያሱ 6፡1-27)

1. በክፍሎቹ ውስጥ የተነገሩትን ነገሮች በየተራ እንዲናገሩ ማበረታታት፡፡
2. ኢያሱ በሙሉ ልብና በእርግጠኛነት ሊናገር ያስቻለውምክንያት በ6፡2 ላይ እግዚአብሄር ለእርሱ ለራሱ ከተማይቱን በእጅህ አሳልፌ ሰጥቻለው ያለውን የተስፋ ቃል ተመስርቶ ነው፡፡
3. በእኔ አመለካከት በጣም ከባድ ትዕዛዝ ነው፤ ምክንያቱም ‹‹አንዲት ቃል›› ከሰው አፍ ሳይወጣ ለብዙ ሰዓታት ቀርቶ ለአንድ ሰዓት እንኳን መቆየት ለብዙዎቻችን ፈተና ነው፡፡ በተለይ ከባድ የሚያደርገው የመጨረሻው ቀን ሰባት ጊዜ ሲዞሩ ያንን ያህል ጊዜ ቃል ከአፍ አለማውጣት በእኔ አስተያየት እጅግ በጣም ከባድ ነው፡፡
4. የተላለፈው ትዕዛዝ በከተማይቱ ውስጥ ያለውን ሁሉ ጨርሶ ማጥፋት ሲሆን በዚህ ውስጥ እንዳይጠቃለል ኢያሱ ለይቶ ያስቀመጠው ነገር ቢኖር ረዓብና ቤተሰቧ ናቸው፡፡
5. በግብጽ ከሞት መልዓክ መዳን፤ ወደ ኖህ መርከብ ውስጥ ገብቶ ማምለጥ፤ በክርስቶስ ውስጥ ገብቶ ከቁጣ ማምለጥ
6. ይህ ‹‹ሰጥቼሃለሁ›› የሚለው ሃሳብ የሚነግረን ነገር ኢያሪኮ በውግያና በሰራዊት ብዛት ወይም በመሪዎች ጥበብ የበላይነት የምትወረስ እንዳልሆነች፤ ነገር ግን የእግዚአብሄር ነጻ ስጦታ መሆኗን ያስገነዝበናል፡፡
7. በሶስተኛ ደረጃ የሰፈረው ስም የረዓብ ስም ነው፡፡ እግዚአብሄር ያከበራት ምክንያት ደግሞ እስራኤላውያን ብዙ ተዓምራትና ድንቅ እያዩ እንኳን ባለማመን ሲቸገሩ ይህች ሴት ግን በተገለጠላት ትንሽ እውነት ለሰማይን አምላክ ካሳየችው ታላቅ እምነት የተነሳ ነው፡፡
8. የጦር አበጋዝ አድርጎ በ5፡13-15 ውስጥ ራሱን ያስተዋወቀው እግዚአብሄር ለእስራኤል ልጆች ያዘዘውን የጦር ስልት እንዳለ ታዘዋል፡፡ ትዕዛዙ ያተኮረው ከጦር መሳሪያ ውጭ የሆነ በእምነት ላይ ያተኮረ ነበረ፡፡
9. በ2ኛ ዜና 20፡15እና 17፣ በመዝሙ 46፡10፣ ኤፌ 6፡12ትና በመሳሰሉት ክፍሎች እንደምናየው እግዚአብሄር ለአማኝ ሁሉ በጋርዮሽ የሰጠው የጦር ሥልት ለድላችን በእርሱ ማዳን ላይ ብቻ መታመን እንደሚኖርብን ነው፡፡ ለተቀረው ጥያቄ እያንዳንዱ ተሳታፊ የየግል ሃሳቡን እንዲያካፍል ማበረታታት፡፡

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት ዘጠኝ (ኢያሱ 7፡1-26)

1. የተወሰኑ ሰዎች አጠር አጠር አድርገው እንዲናገሩ ተራ ይሰጥ።
2. በዚህ ቁጥር ላይ ኢያሱ ሰላዮችን ወደ ጋይ ሲልክ ነው የምናየው። በእኔ ግምት ይህ አይነቱ ታክቲክ ቀድሞ ስለሰራ ዛሬም እግዚአብሄር በዚያው መንገድ ይሰራል የሚል የተሳሳተ ግምት ይመስለኛል። ስራው በስለላ ጥራት ሳይሆን ከእርሱ ጋራ ባለ ግንኙነት የሚሰራ መሆኑን ይህ ክፍል ያስረዳናል።
3. ከሰላዮቹ ሪፖርት የሚታየው በጣም የከተማይቱን ሰዎች እንደናቁና በራሳቸው ደግሞ ከሚገባ በላይ የመተማመን ነገር ይታይባቸዋል። በዘኍ 14 ጠላቶቻቸውን አተልቀው እግዚአብሄርን ማሳነሳቸው ጥፋት ሲሆን በዚህ ክፍል ደግሞ ጠላቶቻቸውን አሳንሰው ራሳቸውን ከፍ የማድረጋቸው ጥፋት ይታያል።
4. ቀድሞ ይህ ቃል ለአህዛብ ነገስታት ነበረ ኢያሱ 2፡11 ንና 5፡1ድን ተመልከት። አሁን ግን በእስራኤል ህዝብ ላይ ነው ተፈጻሚነትን ያገኘው፤ ምክንያቱም እርም በውስጣቸው ስላለና እግዚአብሄርን ስላልታዘዙ ነው።
5. ልብሳቸውን ሲቀዱ፤ በግንባራቸው ሲደፉና በራሳቸው ላይ ትቢያ ነሰነሱ። የኢያሱ ሶስት ጥያቄዎች በቁ6-9 ተዘርዝረው ይገናሉ።
6. የመጀመሪያ አጭር መልሱ፡ ‹‹ተነስ በግንባርህ ለምን ተደፋህ›› ነው። ስድስቱ የተዘረዘሩት ነገሮች፡ በድለዋል፤ ጥሰዋል፤ ወስደዋል፤ ሰርቀዋል፤ ዋሽተዋል፤ ደባልቀዋል። የሚሉ ናቸው።
7. ቁ13 ላይ ያለው ‹‹እርም የሆነ ነገር በመካከላችሁ ስላለ ይህንን ካላስወገዳችሁ…›› የሚለው በዚህ መሃል ያደረገውን ቢገልጥ ምናልባት ይቅርታን ያገኝ ይሆናል።
8. የእስራኤል ህዝብ በአጠቃላይ በተስፋ መቁረጥ ተመትተዋል፤ ሰላሳ ስድስት ሰዎች በጦርነቱ ሞተዋል፤ ቤተሰቦቹ በሙሉ ከነከብቶች፤ አህዮች ሁሉ ህይወታቸውን አጥተዋል።
9. እያንዳንዱ የራሱን ሃሳብ ይስጥበት።

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት አስር (ኢያሱ 8፡1-35)

1. እንዳይፈራ፤ እንዳይደነግጥ፤ ሰራዊቱን ሁሉ ይዞ እንዲወጣና ጋይን እንዲወጋ፤ በኢያሪኮ ያደረገውን ሁሉ ደግሞ በጋይ እንዲያደርግ፤ ምርኮውንና ከብቱን ህዝቡ እንዲወስድ እንዲያደርግና የደፈጣ ጦር እንዲያዘጋጅ።
2. በአይ ከተማ ላይ በገጠማቸው ሽንፈት እርሱ ብቻ ሳይሆን ህዝቡ ሁሉ በዚህች ትንሽ ሰራዊት ድል ከተመታን ከፊታችን ያለውን ከባድ ሰልፍ እንዴት እንወጣዋለን የሚለው ሃሳብ ፍርሃት ለቆባቸው ነበረ። ሃጥያት በድፍረት እንዳንመላለስ ያኮላሸናል። የወደቀ ሰው ባለበት እንዳይቀር እግዚአብሄር መልሶ የሚያቆም ምህረት እንዳለውም እናያለን።
3. ጋይን ለመውጋት ኢያሱ ሰራዊቱን በሙሉ ይዞ መውጣቱና፤ የደፈጣ ጦር ማዘጋጀቱ መታዘዙን ያሳየናል።
4. ይህንን አነጋገር የተጠቀመበት ምክንያት በኢያሱ 6፡18-19 ላይ እግዚአብሄር ኢያሪኮን ሲይዙ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ከነገራቸው ሃሳብ ጋራ የሚነጻጸር ሃሳብ ነው።
5. ድል የተመቱ ለመምሰል ነበረ የሸሹት። እግዚአብሄር ነበረ የውግያ ስልቱን የሰጣቸው።
6. ምዕራፍ 6 ተአምራታዊ ድል ሲሆን ሌላው ግን በተለመደው የጦርነት ሥልት ነው ድልን የሰጣቸው። ከዚህ ልንማር የምንችለው ምሪትን ወይም ለችግር መፍትሄን ሲፈልግ በተአምር እርሱ ሲፈልግ ደግሞ ተአምራት በማይጠይቅ መነገድ ሊሰራ እንደሚችል ልንገነዘብ እንችላለን።
7. ያደረጉት የመጀመሪያ ነገር ከተማይቱን ለመኖሪያነት ማመቻቸት ሳይሆን ራሳቸውን ለአምልኮ ማዘጋጀት ነበረ። በእግዚአብሄር የተገኘውን ድል እንደምናምን ሳንቆጥር የሚገባውን አምልኮ በቅድሚያ ልናስረክበው ይገባናል የሚለውን ሃሳብ እናገኛለን።
8. ቁ30-35ትን ለመረዳት እነዚህ ክፍሎች የሚረዱን፡ ገሪዛን የበረከትና ጌባል ደግሞ የእርግማን ተራራዎች እንደሆኑ፣ መሰዊያው ደግሞ የተሰራው በጌባል ማለትም በእርግማን ተራራ ላይ እንጂ በገሪዛን ላይ እንዳልሆነ(እርግማን ያለበት እንጂ በበረከት ወስጥ ያለ መስዋዕት አያስፈልገውምና ነው።)
9. ጠላቶቻቸው ሽሽታቸውን ሲያዩ የበለጠ ጦር ማሰፍ ነው የጀመሩት።

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት አስራ አንድ (ኢያሱ 9:1-27)

1. አምስት ነገስታት በአንድነት ሆነው የእስራኤልን ህዝብና ኢያሱን ሊወጉ እንደወጡ ይታያል። እዚህ ላይ የተጠቀሱትና በዘጸ 23:23 ላይ ያሉት ዝርዝራቸው አንድ ነው።
2. ይህንን ድፍረት ያገኙበት ዋና ምክንያት በአካን ሃጥያት ምክንያት ጋይን በምታህል ሀገር መሸነፋቸው ለካስ ሲሸነፉ ይችላሉ ወደሚለው ድፍረት አመጣቸው። የምንማረው ነገር ቢኖር የአካን ሃጥያት ካስከተለው ነገሮች አንዱ ለጠላት የልብ ልብ መስጠቱ ነው።
3. የጋይ ሰዎች ከሩቅ እንደመጡ አድርገው እነኢያሱን ለማታለል ፈለጉ? ምክንያቱም በአካባቢው ያሉትን መንግሥታት ሁሉ ሊያጠፉ እንደመጡ ስለገባቸው ነው።
4. በገባዖን የሚኖሩት ሰዎች ኤዊያውያን ሲሆኑ በዘጸ 23:32 ውስጥ እግዚአብሄር አንድ ሳያስቀሩ እንዲያጠፏቸው የተነገረላቸው ሰዎች እንደሆኑ እናነባለን።
5. ቢያንስ አንድ ሰው ከቁ7-13 የተካሄደውን በአጭሩ እንዲናገር ይሁን። እነዚህ ሰዎች ከረዓብ ጋራ የሚመሳሰሉት፡ ሁለቱም የእግዚአብሄርን ዝና ሰምተዋል፣ ሁለቱም ዋሽተዋል፣ ሁለቱም በህይወት የመኖር ፍላጎት ነበራቸው፣ ሁለቱም እግዚአብሄር ያለውን እንደሚያደርግ እምነት ነበራቸው (9:24)።
6. አስቀድመው እጅግ ሩቅ ከሆነ ቦታ መምጣታቸውን ስለተናገሩና ኢያሪኮንና አይን ከጠቀሱ መንገድ ላይ እንዳልነበሩና በአካባቢው እንደሚኖሩ እንዳይታወቅባቸው ነው።
7. ለቀረበላቸው ያደረጓቸው ሁለት ነገሮች፡ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መልሳቸውን መስማትና አመጣን ካሏቸው ነገሮች ናሙና በመውሰድ ተክክለኛነቱን ማረጋገጥ ነበረ። ያላደረጉት እግዚአብሄርን መጠየቅ ነበረ። ስህተታቸውን ያወቁት ከ3 ቀናት በኋላ ነበረ።
8. ይህ የገባዖን ሰዎች የተገባላቸው ቃል ኪዳን በማጭበርበር ቢሆንም እንኳን ከእነዚህ ሁለት ክፍሎች እንደምንመለከተው ምን ያህል እግዚአብሄር በስሙ የተገባ ቃል ኪዳን እንዲታጠፍ እንደማይፈቅድና ቃልኪዳኑን በቸልታ ማየት ደግሞ ትልቅ ዋጋን ሊያስከፍለን እንደሚችል እናያለን። የተቀረውን እያንዳንዱ ሃሳብ ይስጥበት።

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት አስራ ሁለት (ኢያሱ 10፡1-28)

1. አዶኒጼዴቅና ህዝቡ የደነገጡት፡ አንደኛ ኢያሱ ጋይን እንደደመሰሳት ሌላው ደግሞ የገባዖን ሰዎች ከእስራኤል ጋራ ቃልኪዳን ማድረጋቸውን ስለሰሙ ነው፡፡ ክፍሉ ገባዖን ታላቅ ከተማ እንደሆነች፣ ሥፋቷ ከጋይ እንደሚበልጥና ሰዎቿም ብርቱ ተዋጊዎች እንደሆኑ ይናገራል፡፡
2. ቃል ኪዳን መግባታቸው ያስከተለባቸው፣ ጠላታቸው በሙሉ ኃይሉ ተነሳባቸው፡፡ እኛም ጌታን ለመከተል ቃል ኪዳን ስንገባ ጠላታችን ዝም ብሎ አለማየቱ ያመሳስላቸዋል፡፡ እነሱ ያደረጉት ቃል ወደገባላቸው ሰው መልዕክት አስተላለፉ፤ እኛም ጠላታችን ሲያጠፋን ሲነሳብን ቃል ወደገባልን አምላክ ነገራችንን ማስተላለፍ እንደሚኖርብን እንማራለን፡፡ (መዝ 119፡94)
3. እግዚአብሄር አስፈልጊውን ማበረታቻ ሰጥቷል፣ የውጊያው ፍጻሜ ምን መሆኑን አስታውቋል በጠላቶቻቸው ላይ ሽብር ዘርቷል፣ የበረዶ ድንጋይ አውርዷል፤ ኢያሱ ደግሞ፡ ምርጥ ሰራዊት አዘጋጅቷል፣ ሌሊቱን ሁሉ ሲገሰግስ አድሯል፡፡ ከዚህ የምንማረው እግዚአብሄር ድል ታደርጋለህ ብሎ ቃል ገባ ማለት ለስንፍና በር መክፈቱ እንዳልሆነና አስፈላጊውን የማድረግ ሃላፊነት እንዳለብን ያስገነዝበናል፡፡
4. በኢያሪኮ የህዝቡ ተሳትፎ በጣም ውስን ነው፣ የጋይን ጦርነት በተመለከተ ከእግዚአብሄር ከበስተኋላ እንደሚሰራ ቢታወቅም ጦርነቱ ሙሉ ለሙሉ የተካሄደው በሰራዊቱ ይመስላል፣ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ እግዚአብሄርና ህዝቡ በቅንጅት የጋራ ጦርነት ሲያካሂዱ ይታያል፡፡
5. ጦርነቱን የእግዚአብሄር የሚያሰኙት ሃሳቦች፡ በቁ11 ላይ ግልጽ ሆኖ ከሚታየው ከበረዶው ድርጊት ሌላ፣ አሸበራቸው፣ መታቸው፣ ተከተላቸው፣ አሳዶ መታቸው፣ የበረዶ ድንጋይ አወረደበቸው፣ የሚሉትን ሁሉ ስናይ ጦርነቱ በእርግጥም የእግዚአብሄር እንደነበረ እናያለን፡፡
6. አሞራዊያን እየተመቱ ባሉበት ሰዓት ፀሐይና የጨረቃ እነርሱን ለመርዳት ቶሎ መጥለቅና መጨለም ሲገባቸው ለጠላቶቻቸው ብርሃን መስጠት መቀጠል እንዳልረዷቸው ሲያሳይ በሌላ በኩል ደግሞ የእስራኤል አምላክ ፀሐይንና ጨረቃን የሚቆጣጠር እውነተኛ አምላክ መሆኑን ሊገነዘቡ ይችላሉ፡፡
7. ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ የምላቸው፤ የመጀመሪያው ሌሎቹ ጠላቶቻቸው ሰምተው ፍርሃት እንዲሞሉ ሲሆን ሌላው ደግሞ እስራኤላውያን ድፍረትና እምነት እንዲሞሉ ነው፡፡
8. እነዚህን ሰዎች ብልህ ሊያሰኛቸው የሚችለው ነገር ቃል ኪዳን ያላቸው ከብርቱ ህዝብ ጋራ መሆኑን ማወቃቸውና በራሳቸው ለመወጣት ሳይሞክሩ በቶሎ እርዳታ መጠየቃቸው ነው፡፡ ሌሎቹ ጥያቄዎች እያንዳንዱ የራሱን ሃሳብ ይስጥባቸው፡፡

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት አስራ ሶስት (ኢያሱ 14፡1-15)

1. ካህኑ አልአዛር፣ ኢያሱና የየነገዱ ጎሳ አባቶች ነበሩ። ርስቱን የተከፋፈሉትም እግዚአብሄር ለሙሴ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ነበረ።
2. በዚህ ርስት ክፍፍል ውስጥ ያልገቡት ሁለት ነገድ ተኩሎቹና የሌዊ ነገድ ናቸው። ሁለት ነገድ ተኩሉ ከዮርዳኖስ በስተ ምስራቅ በሙሴ እንደተነገረው ርስታቸውን የተቀበሉ ስለሆኑና የሌዊ ወገን ደግሞ ርስታቸው እግዚአብሄር እንደሆነ ስለተነገራቸው ርስትን አልተካፈሉም።
3. ካሌብ ሃሳቡን የከፈተውና መሰረት አድርጎ የተነሳው የእግዚአብሄርን የተስፋ ቃል በመጥቀስ ነበረ። ከዚህ እኛም ልንማር የምንችለው ነገራችንን በእግዚአብሄር ቃል ላይ መመስረት ነው።
4. ትክክለኛ ማስረጃ ማምጣቱን፣ አምላኩን በፍጹም ልቡ እንደተከተለ፣ እግሩ የረገጠው ቦታ ሁሉ እንደሚሰጠው። ለተናገራቸው ነገሮች እውነትነት ሊመሰክር የሚችል ከእግዚአብሄር በስተቀረ ከህዝቡ ሁሉ መሃል አንድ ሰው ብቻ ሲሆን፤ ያም ሰው በስለላው አብሮት የተሳተፈውና የረጅም ዘመን ጓደኛው ኢያሱ ብቻ ነው።
5. ትክክለኛ ማለቱ እውነተኛ ማለቱ አይደለም፤ ምክንያቱም ለአውነተኛነቱ ከሆነ አስሩም ያመጡት ማስረጃ ልክ ካሌብ ያመጣው አይነት ነበረ፤ ነገር ግን በሁለቱ መካከል የነበረው ልዩነት ካሌብ ከተመለከተው ሁኔታ በላይ የሆነውን አምላክ ማየት ሲችል እነርሱ ግን የሁኔታው አስፈሪነት ትልቁን አምላክ ማየት እንዳይችሉ አይኖቻቸውን ከልሎታል።
6. እግዚአብሄር በመልካም ይናገርለት እንጂ ካሌብ ከእግዚአብሄር መልካምነትና ጥበቃ የተነሳ አድርጎ ስለሚያምን ቀሪው ህስብ እየሰማ ክብሩን ለእግዚአብሄር ሲሰጥ ቁ10 ላይ እናያለን። ምንም ያህል ከፍ ብንል፣ ያሰብነው ቢሳካልንና ትልቅ ደረጃ ብንደርስ ከሰዎች ስለተሻልን ሳይሆን ከአምላካችን በጎነት የተነሳ እንደሆነ እንዳንዘነጋ ያስተምረናል።
7. ይህንን ስለካሌብ የመሰከሩት፡ ሙሴ፣ ኢያሱ፣ ካሌብ ራሱና እግዚአብሄር ናቸው።
8. ካሌብ የነበሩትን ሁኔታዎች ከባድነታቸውን አይክድም፣ አምላኩን ደግሞ በፊቱ ካሉት ሁኔታዎች ሁሉ በላይ እንደሆነ የተረዳ ሰው ነው። በዚህ ክፍልና በቀድሞው በካሌብ ያለው ልዩነት ቢኖር የእድሜ ብቻ እንደሆነ ይታያል።
9. በዚህ ሰው ህይወት የተለያዩ መልካም ነገሮችን ማየት ቢቻልም፤ አንዱ ጎልቶ የሚታየው ነገር ከሁኔታዎች ሁሉ በላይ አምላኩን አተልቆ ማየት መቻሉ የሚያስቀና ህይወት ነው።

# ለመሪው የተዘጋጀ

## (ሀ) ጥናት አስራ አራት (ኢያሱ 17፡1-18)

1. ሰለጰዓድ አምስት ሴቶች ልጆች እንደነበሩትና የማን ልጅ እንደነበረ እናውቃለን። የዚህ ሰው ሴቶች ልጆቹ የገጠማቸው ሁኔታ አባታቸው ወንድ ልጅ ስላልወለደና ሁሉም ሴቶች ስለሆኑ የአባታቸውን ርስት ለመቀበል አለመቻላቸው ሲሆን፤ ስለሁኔታውም ያደረጉት ነገር ቢኖር በቀጥታ ነገሩ ወደሚመለከተው አካል በመሄድ ሁኔታውን በግልጽ ማስረዳት ነበረ።
2. እነዚህ ሴቶች ወደሚመለከታቸው ሰዎች ከመሄድ ይልቅ በአካባቢያቸው ላሉት ሰዎች ሃሜት ሊያባዙ ወይም ስለሆነው ነገር ሊያጉረመርሙ፣ ወይም ደግሞ ቲፎዞ ሊያስተባብሩ ይችሉ ነበረ። ከዚህ ልንማር የምንችለው፤ ሰዎች በሚያደርጉት ነገር የማንስማማበት ነገር ሲኖረን በቀጥታ ነገሩ የሚመለከታቸውን ሰዎች በመሄድ ማነጋገር እንደሚኖርብን ነው።
3. በቁ4 መነሻ አድርገው የቀረቡት እግዚአብሄር አስቀድሞ ተስፋ በገባው ነገር ላይ ሲሆን፤ በቁ14 ላይ ግን (logical/fair) በሆነ አመለካከት ላይ ተመርኩዞ እንዲሰጣቸው ነው የሚጠይቁት። ኢያሱ ለመጀመሪያው ጥያቄ ፈጣን ምላሽ የሰጠበት ምክንያት እግዚአብሄር የተናገረው ነገር ስለነበረ ምንም ዓይነት ውይይት ወይም ምላሽን መስጠት አላስፈለገውም።
4. እነዚህ አምስት ሴቶች አጥተውት የነበረውን ርስታቸውን ለማግኘት ዋነኛ ምክንያት የሆነው ነገር እግዚአብሄር የተናገረውን አተኩሮ መስማት፣ አለመዘንጋት፣ ችላ አለማለትና ለቃሉም የሚገባውን ቦታ በመስጠት በአስፈላጊው ሥፍራም በሥራ ላይ ለማዋልም አለመፍራት ነው።
5. በዚህ ክፍል የዮሴፍ ዘሮች የብረት ሰረገላ ያላቸውን ከነዓናውያን እንደፈሩ ስናይ በኢያሱ 14፡12 ላይ ካሌብ ግን የሚያስፈሩና የተመሸጉ ከተሞች ቢሆኑም በእግዚአብሄር እርዳታ እንደሚያሸንፋቸው በእርግጠኛነት ነበረ የሚናገረው።
6. ድርሻው አልበቃንም ላሉት የኢያሱ ምላሽ ‹‹ወጥታችሁ ለራሳችሁ መንጥሩ›› የሚል ነበረ። ሰዎቹ የመለሱለት ከነዓናውያን የብረት ሰረገሎች አሏቸው የሚል የፍራቻ ቃል ነበረ። እኛም ብዙ ጊዜ በጌታ ማደግን እንፈልጋለን ጊዜ ወስደን መ/ቅዱሳችንን ማንበብ አንፈልግም፣ ጌታን ማገልገል እንፈልጋለን ነገር ግን ሰዓታችንን አክብረን ለመገኘት አንፈልግም፣ ለጌታ ታማኞች ለመሆን እንፈልጋለን ነገር ግን አስፈላጊውን ቼክ ለመጻፍ እጃችን እሺ አይለንም…ወዘተ
7. ኢያሱን የሰዎቹ ፍርሃት ሃሳቡን አላስቀየረውም። ለችግራቸው የሰጣቸው መፍትሄ ያኔ ምድራቱን ሰልሎ ሲመለስ ለህዝቡ የሰጣቸውን መልስ ነበረ፤ ይኸውም ‹‹ ከነዓናውያን የብረት ሰረገላ ቢኖራቸውና ብርቱዎች ቢሆኑም እንኳ ከዚያ ታስወጧቸዋላችሁ›› የሚል ነበረ።
8. መጠየቃቸው ስህተት አልነበረም፤ ነገር ግን ያልተረዱት አንድ ነገር ቢኖር የፈለጉትን ነገር ለማግኘት መስዋዕት መክፈል እንዳለባቸው ነው። ለተቀረው መልስ እያንዳንዱ ሰው ሃሳቡን ያካፍል።

# ለመሪው የተዘጋጀ

## (ለ) ጥናት አስራ አራት (ኢያሱ 17፡1-18 ዘኁ 27፡1-8)

1. ሰለጰዓድ አምስት ሴቶች ልጆች እንደነበሩትና የማን ልጅ እንደነበረ እናውቃለን፡፡ የዚህ ሰው ሴቶች ልጆቹ የገጠማቸው ሁኔታ አባታቸው ወንድ ልጅ ስላልወለደና ሁሉም ሴቶች ስለሆኑ የአባታቸውን ርስት ለመቀበል አለመቻላቸው ሲሆን፤ ስለሁኔታውም ያደረጉት ነገር ቢኖር በቀጥታ ነገሩ ወደሚመለከተው አካል በመሄድ ሁኔታውን በግልጽ ማስረዳት ነበረ፡፡
2. ክፍሉ የሚናገረውን ነገር ቢያንስ ሁለት ሰዎች በራሳቸው አገላለጽ እንዲናገሩ እድል ይሰጣቸው፡፡
3. ሙሴ ጥያቄው ሲቀርብለት ያደረገው ነገሩን ወደ እግዚአብሄር መውሰድ ነው፡፡ ኢያሱ ግን መልሱን እግዚአብሄር ለሙሴ የተናገረ ስለሆነ መታዘዝ እንጂ እንደገና መውሰድ አላስፈለገውም፡፡ ከዚህ ልንማር የምንችለው ትምህርት፤ እግዚአብሄር በቃሉ የተናገረው ነገር ካለ ያንን መታዘዝ እንጂ እግዚአብሄርን ምን ላድርግ ብሎ መጠየቅ አስፍላጊ እንዳልሆነ እንማራለን፡፡
4. እነዚህ ሴቶች ወደሚመለከታቸው ሰዎች ከመሄድ ይልቅ በአካባቢያቸው ላሉት ሰዎች ሃሜት ሊያባዙ ወይም ስለሆነው ነገር ሊያጉረመርሙ፣ ወይም ደግሞ ቲፎዞ ሊያስተባብሩ ይችሉ ነበረ፡፡ ከዚህ ልንማር የምንችለው፤
5. እነዚህ አምስት ሴቶች አጥተውት የነበረውን ርስታቸውን ለማግኘት ዋነኛ ምክንያት የሆነው ነገር እግዚአብሄር የተናገረውን አተኩሮ መስማት፣ አለመዘንጋት፣ ችላ አለማለትና ለቃሉም የሚገባውን ቦታ በመስጠት በአስፈላጊው ሥፍራም በሥራ ላይ ለማዋልም አለመፍራት ነው፡፡
6. በቁ4 መነሻ አድርገው የቀረቡት እግዚአብሄር አስቀድሞ ተስፋ በገባው ነገር ላይ ሲሆን፤ በቁ14 ላይ ግን (logical / fair) በሆነ አመለካከት ላይ ተመርኩዞ እንዲሰጣቸው ነው የሚጠይቁት፡፡ ኢያሱ ለመጀመሪያው ጥያቄ ፈጣን ምላሽ የሰጠበት ምክንያት እግዚአብሄር የተናገረው ነገር ስለነበረ ምንም ዓይነት ውይይት አላስፈለገውም፡፡
7. ሴቶችም በእስራኤላዊያን መሃል ርስት እንዲኖራቸው እግዚአብሄር አወጀ፡፡ ከዚህ ልንማር የምንችለው አንድ ነኝ ወይም ጥቂቶች ነን ብለን እንደ እግዚአብሄር ሃሳብ የሆነውን ነገር ማዳፈን እንደሌለብንና እግዚአብሄር ለተናገረው ነገር በጽናት መጋፈጥ እንደሚኖርብን እንማራለን፡፡
8. ይህ አካሄዳቸው ጥበብ የተሞላው ነበረ ማለት የሚያስችለን፤ ሌሎችን ወደ ሐሜትና ወደ ቡድን ስሜት ውስጥ አላስገቡም፣ የእግዚአብሄርን ቃል በሥራ የሚውል ነገር እንጂ ቃል ብቻ እንዳልሆነ መገንዘባቸውና በጊዘው በህብረተሰቡ ተቀባይነት የሌለው ሃሳብ ይዘው መቅረባቸው ድፍረትና ብልህነት ነው፡፡ ሰዎች በሚያደርጉት ነገር የማንስማማበት ነገር ሲኖረን በቀጥታ ነገሩ የሚመለከታቸውን ሰዎች በመሄድ ማነጋገር እንደሚኖርብን እንማራለን፡፡

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት አስራ አምስት (ኢያሱ 22፡1-34)

1. ታዛዥነታቸው ለሙሴ፣ ለኢያሱና ለእግዚአብሄር ነበረ፡፡ የእነዚህን ሰዎች ታማኝነት ልዩ ሊያሰኘው የሚችለው ነገር ‹‹ከረጅም ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ›› የሚለው ሃሳብ ሲሆን፤ ለራሳቸው የተደላደለ፣ ጦርነት የሌለበት ኑሮ መኖር ሲችሉ ለብዙ ዓመታት ከወንድሞቻቸው ጋራ መቆማቸው ትልቅ ታማኝነት ነው፡፡ካሌብ በስለላ ሲሰማራ የ40 ዓመት ሰው ሲሆን ተጨማሪ 40 ዓመታት በምድረ በዳ ከዞሩት ጋራ 80ዓመታት፤ መሬት ክፍፍል ሲጀመር 85 ከሆነው እነዚህ ሰዎች ቢያንስ ለ5 ዓመታት ወንድሞቻቸውን በጦርነት ረድተዋል ማለት ነው፡፡
2. አምላካቸውን እግዚአብሄርን እንዲወዱ፣ በመንገዱ ሁሉ እንዲሄዱ፣ ትዕዛዙን እንዲፈጽሙ፣ አምላካቸውን አጥብቀው እንዲይዙት፣ በፍጹም ልባቸውና በፍጹም ነፍሳቸው እንዲያገለግሉት
3. ሁለት ተኩሉ ነገዶች ወደ ርስታቸው ወደ ገለዓድ ምድር ተመለሱ፤ ግዙፍ መሰዊያ ሰሩ፤ እስራኤላውያን መሰዊያ መስራታቸውን ሰሙ፤ ዘጠኝ ተኩሉ ነገድ ለጦርነት በሴሎ ተሰበሰቡ፡፡ መሰዊያው የተሰራው በዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ፣ በእስራኤላውያን ይዞታ በገሊሎት ነበረ፡፡
4. እስራኤላውያን የወሰዱት እርምጃ ወደ ወንድሞቻቸው መልዕክተኞችን መላክ ነበረ፡፡ ለዚህም ተልዕኮ የተመረጡት፡ የካህኑ አልዓዛር ልጅ ፊንሃስና ከጎሳዎቹ የተውጣጡ አስር ሰዎች ነበሩ፡፡ እነዚህ ሁለት ተኩል ነገዶች እግዚአብሔረ የሚጸየፈውን ባዕድ አምልኮ እንደጀመሩ ያመኑ ሲሆን የዚህን ዓይነት ሃጥያት በማጽዳት ፊንሐስ እግዚአብሄር የመሰከረለት ሰው መሆኑ ተነግሮለታል፡፡ መዝ 106፡30-31
5. ፊንሃስና ከእስራኤል የተላኩት ሰዎች መሰዊያ ሰሩ ለተባሉት ሰዎች አምላክን እንደካዱ፣ ወደኋላ እንዳሉና በእግዚአብሄር ላይ እነዳመጹ በእርግጠኛነት ይነግሯቸዋል፡፡ የነፊንሃስን አቀራረብ ስንመለከት ያዕ1፡19 በሥራ ላይ አልዋለም ማለት የምንችለው፤ ሰዎቹ ለመስማት ምንም ጊዜ ሳይሰጡ ለመናገር መፍጠናቸው ከያዕቆብ ምክር በተቃራኒ ሄደዋል ደግሞም የደረሱበት የመደምደሚያ ሃሳብ ስህተት ነበረ፡፡
6. ምክንያቱም በዘሌ 17፡3-4 መሰረት መስዋዕት ሊቀርብ የሚችለው በአንድ ቦታ ብቻ ነው፤ ይኸውም መገናኛው ድንኳን ባለበት ሥፍራ ነው፡፡
7. መሰዊያው የተሰራበት ትክክለኛ ምክንያት ወደፊት የልጅ ልጆቻቸውን የእስራኤል ልጆች እናንተ ያላችሁት ከዮርዳኖስ ባሻገር ስለዚህ ከእስራኤል አምላክ ከእግዚአብሔር ጋራ ድርሻ የላችሁም የማለት ነገር ቢመጣ ምስክር እንዲሆን የተሰራ ነው፡፡ እነርሱ ከተናገሩት ሃሳብ ጋራ ምንም የማይገጣጠም ነገር ነው፡፡ በዘሌ 17፡3-4 ያለውን ህግ ጠንቅቀው ያውቁታል፡፡
8. እስራኤላውያን በቀጥታ ጦርነት ከማወጃቸው በፊት ወደ ወንድሞቻቸው መልዕክተኛ መላካቸው መልካም ነግር ሲሆን ሳያረጋግጡ በእግዚአብሄር ላይ አምጻችኋል ብለው መናገራቸው አጥፍተዋል፤ የተቀረውን እያንዳንዱ ሰው ለራሱ መልስ ይስጥበት፡፡

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት አስራ ስድስት (ኢያሱ 23፡1-16)

1. እግዚአብሄር እስራኤልን ከጠላቶቻቸው እንዳሳረፋቸውና ይህም ረጅም ጊዜ እንደሆነው ሲነግረን ስለ ኢያሱ ደግሞ በእድሜ በጣም እንዳረጀ እንረዳለን፡፡
2. ኢያሱ ስለራሱ በእድሜ እንደገፋና በጣም እንዳረጀ ነው የሚናገረው፡፡ ኢያሱ በእርጅናው አፉን ሞልቶ መናገር የሚያስደፍረው ምክንያት ዘመኑን በሙሉ የጨረሰው አምላኩን በማገልገል ስለነበረ በከንቱ የደረሰበት ሽምግልና ስላልነበረ የሚያኮራው እንጂ የሚያሳፍረው አልነበረም፡፡
3. ከነዓን በሚኖሩ ህዝቦች ላይ ድል መስጠቱን፣ እርሱ ስለህዝቡ እንደተዋጋም እናያለን፣ የተቀረውንም ምድር ሁሉ እርሱ ተዋግቶ እንደሚያወርሳቸው ይነግራቸዋል፡፡ በጠላቶቻቸው ላይ ላደረገው ነገር ሁሉ በተዘዋዋሪ ሳይሆን በአይናቸው ያዩት ነገር እንደሆነ ያስገነዝባቸዋል፡
4. እግዚአብሄር ራሱን ኢያሱን በመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ ያጽናናበትን ቃላቶች ነው በዚህ ጊዜ ኢያሱ ለህዝቡና ለአለቆቹ እየተጠቀመ ለማበረታታትና ለማጽናናት እየተጠቀመ ያለው፤ ይህንንም ስናነብ ሊታወሰን የሚገባው የአዲስ ኪዳን ጥቅስ 2ኛ ቆሮ 1፡3-7 ነው፡፡
5. እንዲበረቱ፣ የሙሴን ህግ እንዲጠብቁ፣ በከነዓን ከሚኖሩት ጋራ እንዳይተባበሩ፣ አማልክቶቻቸውን እንዳይጠሩ፣ በአማልክቶቻቸው እንዳይምሉ፣ አማልክቶቻቸውን እንዳያገለግሉ፣ እንዳይሰግዱላቸውና አምላካቸውን አጥብቀው እንዲይዙ ያስጠነቀቃቸው ሲሆን እነዚህ ሁሉ በሁለት ዓ/ነገር ስንጠቀልል፤ ከአምላክህ ከእግዚአብሄር ጋራ ተጣበቅና በዙሪያህ ካሉት ህዝቦች ራስህን ለይ ማለት ይቻላል፡፡
6. ታላላቅና ሃያላን ህዝቦችን አሳዶላቸዋል፣ እስከዛሬም የተቋቋማቸው የለም፣ ወደፊትም አንዱ ሺውን ያሳድዳል፡፡ ለዚህ እግዚአብሄር ላረገላቸው ነገር ምላሽ የተጠየቁት አምላካቸውን እግዚአብሄርን እንዲወዱት ነው፡፡
7. ይህ ክፍል በተለይ (ብትተባበሩ፣ በጋብቻ ብትተሳሰሩ፣ ብትቀላቀሉ) የሚሉት አነጋገሮች በጋብቻ መጣመርን የሚጠቁም ይመስላል፡፡ ይህ በዘመናችንም ቢሆን ያመነው የእግዚአብሄር ህዝብ ካላመነው ጋራ በትዳር መተሳሰርን በተለያዩ ቦታዎች ስለሚከለክል ለኛም ሙሉ ተፈጻሚነት እንዳለው እንረዳለን፡፡
8. ከነዚህ ቁጥሮች የምንማረው እግዚአብሄር ቃል ከገባ የሚያደርግ አምላክ እንደሆነ ሲሆን ቃሉን የሚጠብቀው በመልካሙ ብቻ ሳይሆን ፍርዱንም እንደሚጠብቅ ያስተምረናል፡፡ ተስፋ እንጠብቃለን ስንል በቃሉ ስለተጻፈ ተስፋ እንደሆነ ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ ለመጥቀስ የጌታ መመለስ ሁላችንም የምንጠብቀው ተስፋችን ነው፡፡

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት አስራ ሰባት (ኢያሱ 24፡1-13)

1. የአብርሃም፣ የይስሐቅንና የያዕቆብን ዕድሜ ብቻ እንኳን በመደመር የዮሴፍን ሳንጨምር ቢያንስ ከ350-400 አመታቶችን ያጠቃልላል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ዘፍ 12 እስከ ዘፍጥረት መጨረሻን ይጠቀልላል፡፡
2. ‹‹እኔ ግን…›› ብሎ እግዚአብሄር የአብርሃም ህይወት የተለየ እንዲሆን የወሰነው እርሱ እንደሆነና ከእርሱ የተነሳ ልዩ መሆኑን እንመለከታለን፡፡ እግዚአብሄር ከወንዙ ማዶ ምድር በማምጣት ወደ ከነዓን መራው፣ ዘሮቹን አበዛለት፣ ይስሃቅን ሰጠው…፡፡ አብርሃም በዚህ ሁሉ የነበረውን አስተዋጽዖ ክፍሉ አይነግረንም፡፡
3. በትንሹ 40 ዓመታትን ይጠቀልላል፡፡ ሙሴንና አሮንን ላከላቸው፣ ግብጻውያንን አስጨንቆ ህዝቡን አወጣ፣ በግብጻውያንና በህዝቡ መሃል ጨለማ እንዲገባ አደረገ፣ ጠላቶቻቸውን በባህር አሰጠመላቸው፣ በምድረ በዳ ለረጅም ዓመታት መኖር እንዲችሉ አደረጋቸው፡፡
4. በቁ8-10 እግዚአብሄር ለህዝቡ ያደረጋቸው ሁለት ትላልቅ ነገሮች፤ አንዱ አሞራዊያንን አጥፍቶ ምድራቸውን መስጠቱና ሁለተኛው ደግሞ የበለዓምን እርግማን ወደ በረከት መለወጡ ናቸው፡፡ የበለዓም ያልተሰማበት ምክንያት በዘኍልቁ እንደምናነበው አንድ ጊዜ የተባረከን ህዝብ ሊረግም የሚችል ስለሌለ ነው፡፡
5. የኢያሪኮ ሰዎች እንደወጓቸውና እግዚአብሄር ደግሞ ተርብ ልኮ ከፊታቸው እንዳሳደዳቸው እናነባለን፣ ለህዝቡ የሚያሳስባቸው እውነቶች፡ በመጀመሪያ ደረጃ ድል ማድረጋቸው በሰይፋቸውና በቀስታቸው እንዳልሆነ፣ የሚኖሩባቸው ከተሞች ያልደከሙባቸውና ያልሰሯቸው እንደሆኑ እንዲረዱና እንዲሁም ካልተከሉት ወይንና ተክል እየበሉ እንዳሉ ያስገነዝባቸዋል፡፡
6. የ5ትና የ6መቶ ዓመታቱን ታሪክ እግዚአብሄር በዚህ ጊዜ ማስታወስ የፈለገው አሁን ተደላድለው በሚኖሩበት በሰጣቸው ምድር እርሱን ረስተው ወደ ሌላ አምልኮ ዘወር እንዳይሉ እንዲሁም ያገኙት ነገር ሃብትም ሆነ ድል ሁሉ ከእርሱ የተነሳ እንደሆነ ሊያስታውሳቸው ነው፡፡ ‹‹እኔ ግን›› ቁ3፣ 8ትና 10 ተመልከት፡፡ በብዙ በተለያዩ መንገዶች መጭመቅ ቢቻም ዋናው ሃሳቡ ‹‹የእግዚአብሄር ታማኝነት›› ማለት ይቻላል፡፡
7. ምንባቡ የጀመረው በአብርሃም ታሪክ ሆኖ እነዚህ የተጠቀሱት በረከቶች ሁሉ ደግሞ በተገባለት የተስፋ ቃል መሰረት የሆነላቸው ለእርሱ ዘሮች ነው፡፡ እርግማኑ ሐረግ የተበጠሰው እግዚአብሄር ለእርሱ በለየው ሰዓት ነበረ፡፡
8. እያንዳንዱ የሚሰማውን ሃሳብ ያካፍል፡፡

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት አስራ ስምንት (ኢያሱ 24፡14-33)

1. እግዚአብሄርን እንዲፈሩ፣ በፍጹም ታማኝነት እንዲገዙለት፣ ሌሎች አማልክትን ከእነርሱ እንዲያርቁና እግዚአብሄርን ብቻ እንዲያመልኩ ነው የጠየቃቸው፡፡
2. በእኔ አመለካከት ‹‹ብቻ›› የሚለው ቃል ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው ያስፈልጋል እላለሁ፤ ምክንያቱም ህዝቡ እግዚአብሄርን ማምለካቸውንና መስዋዕት ማቅረባቸውን ሳይተው ሌሎችን አማልክት በእርሱ ላይ ጨምረው ማምለካቸው ነው ትልቁ ችግር፡፡
3. ሮሜ ከምዕራፍ አንድ አንስቶ እስከ ምዕራፍ አስራ አንድ መጨረሻ ድረስ እግዚአብሄር ለአይሁድና ለአህዛብ ያደረገውን ትልቅ ምህረትና ቸርነት በዝርዝር እንዲረዱ ካደረገ በኋላ ከዚያ በመነሳት ለዚያ ምላሽ እንዲሰጡ በመጠየቅ ም12 እንደሚጀምር ይህም ክፍል አቀራረቡ ያንን የተከተለ በመሆኑ ሁለቱ ክፍሎች ተመሳሳይ ጸባይ አላቸው ማለት ይቻላል፡፡ እነዚህ ክፍሎች መረዳት/እውቀት  ከመስጠት (commitment) መቅደም እንደሚኖርበት ያስተምሩናል፡፡
4. የህዝቡ ምላሽ እግዚአብሄር ብዙ ነገሮችን አድርጎልናል እኛ እናመልካለን አምላካችን ነው የሚል ነበረ፡፡ ኢያሱ ግን የመለሰላቸው እርሱን ማምለክ አትችሉም የሚል ነበረ፤ ምክንያቱም እርሱ ቅዱስና ቀናተኛ አምላክ ስለሆነ፡፡ ይህንን ሲል እነርሱ አምልኮ ብለው በሚቆጥሩት ሌሎች ጋራ እንደተጨማሪ ሆኖ ሊመለክ ስለማይችል በብቸኛነት የሚመለክ የተለየ(ቁዱስ) እና ቀናተኛ(ከሌላ ጋራ ክብሩን የማይካፈል) መሆኑን ሲነግራቸው ነው፡፡
5. እነርሱ እግዚአብሄርን እናመልካለን ብለው ነው የሚያምኑት፤ እርሱ ግን መወገድ ያለባቸው ነገሮች አሉና እርሱን ማምለክ ከፈለጋችሁ እነዚህ መወገድ አለባቸው ይላቸዋል፡፡ ይህ ክፍል የሚጠቁመን ሰዎቹ እግዚአብሄርን ከሌሎች ጋራ በማዳበል የማምለክ ነገር ፈተና እንደሆነባቸው ሲሆን ኢያሱ ደግሞ እየሞከረ ያለው ከዚህ ነጻ እንዲወጡና እንዲላቀቁ ነው፡፡ ቁ14ትን ተመልከት፡፡
6. የሰዎቹ ስም ኢያሱ፣ ዮሴፍና አልአዛር ናቸው፡፡ስለ ሶስቱም የተጻፈው ተመሳሳይ ቃል ‹‹ተቀበረ›› የሚለው ሲሆን ለመቀበር ደግሞ ሶስቱም ሞተዋል ማለት ይቻላል፡፡ ኢያሱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠው ስም ‹‹የእግዚአብሄር ባርያ›› የሚል ነው፡፡
7. እያሱ እየጣረ ያለው እርሱ በመካከላቸው በማይኖርበት ጊዜ ህዝቡ ከእግዚአብሄር ፈቀቅ ብለው አምላካቸውን እንዳይበድሉና እርሱን ብቻ እንዲያመልኩ ለማድረግ ነው የሚችለውን ሁሉ እያደረገ ያለው፡፡
8. የተደረገለትን ከመረዳት የሚያገለግልና የሚያመልከው ሰው ለተደረገለት የፍቅር ምላሽ በደስታ የሚያደርገው ሲሆን ያልተረዳው ግን ከትዕዛዝ የተነሳና በማጉረምረም የሚያደርግ ይሆናል፡፡ ሁሉም የየራሱን ሃሳብ ያካፍል፡፡